# የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ

## መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራም

### ራእይ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ ራእይ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመጣ ፤ የህዝብ ስልጣን ምንጭነት እንዲረጋገጥና እኩልነታቸው በህግ ዋስትና እንዲያገኝ ፤ እንዲሁም የማህበራዊ ፍትህ የሃሳብና የእምነት ነጻነት እንዲኖር ፤እንዲከበርና እንዲረጋገጥ አበክሮ መስራትና መታገል ነው ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዜጎቿ ሲኦል መሆኗን አስቀርቶ ህብረተሰባችን ተቻችሎ ተሳስቦና ተፋቅሮ እንዲኖር ከማድረግ ባሻገር ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ሕዝቡን ማስተባበርና ማደራጀት ያስፈልጋል ብለን እናምናለን ።

## ፤. አላማወቹ

ሀ. ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በግልና መላው ህዝብ በጥቅል ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ያለምንም ገደብ እንዲከበሩለት ይታገላል ።

ለ. የመድብለ ፓርቲ ስርአት እውን እንዲሆንና የመንግስት ስልጣን ከህዝብ ፍትሀዊ ምርጫ ብቻ የመነጨ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረትና ትግል ያደርጋል ።

ሐ. ሁሉም ኢትዮጵያውያን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍሎች ተንቀሳቅሰው የመስራት የመኖርና ንብረት ማፍራት የዜግነት መብታቸው መሆኑን ማረጋገጥ ።

መ. እያንዳንዱ ዜጋ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የትምህርት የጤናና የንብረት ተጠቃሚ እንዲሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ መንደፍ ።

ሠ. ዜጎች ያለማንምና ምንም ተጽእኖ የግልና ነጻ የእምነት ተቋማት እንዲኖራቸዉ በህግ መደንገግ።

ረ. ዜጎች በነጻ የመደራጀት ሰላማዊ ሰልፍና እስከ ስራ ማቆም ትቃውሞ ማድረግ እንደሚችሉ ህጋዊ ዋስትናን  መስጠት ። እንዲሁም የዜጎችን በነጻ የመደራጀት የመጻፍና የመናገር መብት በህግ ማረጋገጥና ማክበር ።

ሰ. ፓርቲያችን ከላይ የተዘረዘሩትን  ራእይና አላማወቹን ለማሳካት በአላማና በትግል ስልቱ ከሚስማሙ ድርጅቶች ጋር ቀርቦ በመነጋገር አስፈላጊውን የህብረትም ሆነ የውህደት ስራ ያከናውናል ።

ሸ. በፓርቲው ፕሮግራም ውስጥ የተካተቱ ፖሊሲወችን ለማስፈጸም እንቅፋት የሚሆኑና የሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅምና አንድነት የሚጎዱ አሁን በአለው ህገመንግስት ውስጥ ተካተው የሚገኙ አንቀጾች በኢትዮጵያ ህዝብ ይሁንታ ተሰጥቶባቸው ማሻሻያ ይደረግባቸዋል ። ወይም ይሰረዛሉ።

ቀ. ከላይ በተራ ቁጥር " ሸ " በተጠቀሰውና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች የሀገሪቱ ህገመንግስት ሀገሪቱንና ህዝቧን በሚመጥን መልኩ በባለሙያ ተጠንቶና በህዝብ ተተችቶ የሚጸድቅ የህገመንግስት ማሻሻያ ይደረጋል ። ይህም ህገመንግስት ወደፊት ግለሰቦች ወይም

ፓርቲወች በስልጣን ላይ ሲወጡና ሲወርዱ እንደፈለጋቸው እንዳይቀያይሩት፤ሰወች የሚቆጣጠሩት ሳይሆን ሰወችን መቆጣጠር የሚችል ጠንካራ ህግ እንዲሆን በቀላሉ ለማሻሻልና ለመለወጥ የማያስችሉ አንቀጾች እንዲካተቱበት ይደረጋል ።

በ. የኢትዮጵያ ህዝብ የተለያየ ቋንቋ ወግና ባህል ያለው ህዝብ ነው ። ይህ ህዝብ ለዘመናት በዚህ ልዩነት ውስጥ አብሮ በመኖር በክፉ በደጉ እየተረዳዳና እየተደጋገፈ እንዲያውም የአንዱ ብሄር ከሌላው በመጋባትና በመዛመድ ተከባብሮና ተጋብሮ የኖረ ህዝብ ነው። የህዝቡ ያለፈ እዉነተኛ ታሪክ ይህ ቢሆንም የዘመኑ ዘረኛ ገዥወች ለራሳቸዉ የስልጣን ማራዘሚያ ሲሉ ህዝቡን በቋንቋ በሀይማኖትና በጎሳ ከፋፍለው እርስ በርሱ እያናቆሩት ይገኛሉ ። ታዲያ የድርጅታችን አንዱ ተልእኮ የሚሆነው ይህን ሰው ሰራሽ የልዩነት አጥር አፍርሶ በምትኩ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋቸው ባህላቸውና ሀይማኖታቸው ተጠብቆ በእኩልነትና በአንድነት የሚኖሩበትን መንገድ መቀየስ ነዉ ።

ተ. ከላይ በተራ ቁጥር "በ" በተጠቀሰውና በተጨማሪም ቀደም ያሉት መንግስታት በተከተሉአቸው የተሳሳቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲወች ምክንያት ላለፉት በርካታ አመታት በህዝቡ ዉስጥ ሰፍኖ የቆየውን የቂም ቁርሾ የበደልና የበቀል ምእራፍን ዘግቶ፤ ወደ ዘላቂና አስተማማኝ የሰላምና የልማት ጎዳና ለመሸጋገር እንዲቻል ፤አንድ ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲወች የሀይማኖት ተቋማት የስቪክ ማህበራትና የሀገር ሽማግሌወች ዉስጥ የተውጣጣ የብሄራዊ እርቅ ኮሚሽን እንዲቋቋም ድርጅታችን የበኩሉን እገዛና ጥረት ያደርጋል ።

## 2. የትግል ስልት

የፓርቲው ዋነኛ የትግል ስልት ሁለገብ ትግል ይሆናል ።ይህ የትግል ስልት መሬት ላይ ያለው ሁኔታ እየተገመገመ ከሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት ይችላል።

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

## 3. የፓርቲዉ ርእዮተአለም

የፓርቲው ርእዮተአለም በሶሻል ዴሞክራሲ ላይ የተመሰረተ ይሆናል ።

## 4. የፖለቲካ ስርአት

4--1 ፓርቲው የሚከተለውና የሚተገብረው የፖለቲካ ስርአት ህገመንግስታዊ መድብለ ፓርቲ ይሆናል ።

4-2 የመንግስት የፖለቲካ ስልጣን ሽግግር የሚደረገው በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ውድድር ብቻ ይሆናል ። ይህም በገለልተኛ አካል የሚመራ ከህዝብ ፈቃድ የሚመነጭና በህግ የበላይነት የሚመራ ነው ።

4-3 ሀገሪቱ ከመንግስት ቁጥጥርና ተጽእኖ ውጭ የሆኑ ስልጣናቸው በህገመንግስቱ የተደነገገ ነጻ ተቋማት ይኖሯታል ። እነርሱም

ሀ. ምርጫ ቦርድ

ለ. ፀረ ሙስና

ሐ. ንብረትና ቁጥጥር

መ. ህግና ሙብት አስጠባቂ ኮሚሽን ናቸው ።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ተቋማት ተጠሪነታቸው ለሀገሪቱ ምክርቤት ይሆናል።

ኢሕብፓ
EPNP
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

## 5. የመንግስት አወቃቀር

5-1. የፌደራል መንግስት ስልጣን በስወስት ዋና ዋና ክፍሎች የተማከለ ይሆናል ። እነርሱም ህግ አዉጭ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈጻሚ ናቸዉ ። እነዚህ ስወስቱ አካላት አንዱ በሌላው ስራ ጣልቃ እንዳይገባ ይሚከለክል ደንብ በህገመንግስቱ ይደነገጋል ።

5-2. ህግ አውጭው ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል ።

5-3. የህዝብ ተወካዮች በህዝብ የሚመረጥና የአገልግሎት የጊዜ ገደብ ያለው ።

5-4. የፌደራሉ አካላት ተወካዮች በህዝብ የሚመረጥና የአገልግሎት ጊዜ ገደብ ያለው ።

5-5. የህግ ተርጓሚ አካሉ ከህግ አስፈጻሚው ተጽእኖ ነጻ ሆኖ እንዲሰራ ተጠሪነቱን የህዝብ በማድረግ በአስፈጻሚው የማይነጠቅ ጠንካራ ስልጣን እንዲኖረው ይደረጋል ። ይህውም የወረዳና የአዉራጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በደንብ ላይ በተደነገገ የትምህርት የልምድና የብቃት ማወዳደሪ ተጣርተው በህዝብ እንዲመረጡና ስራ አስፈጻሚው የማይሾም የማይሽራቸው ሲደረግ የፌደራልና የከፍተኛው ፍርድቤት ዳኞች ግን በስራ አስፈጻሚው ተጥቁመው በምከር ቤቱ እንዲፀድቁ ይደረጋል።

5-6. የሀገሪቱ መሪ በህዝብ የሚመረጥና የስልጣን ዘመኑ በህግ በተገደበ የጊዜ ገደብ የሚሰራ ይሆናል ። የሚመረጠው ባለስልጣን የሚያገለግለው ለአራት አመት ሆኖ በተከታታይ ከሁለት ጊዜ የአገለግሎት ዘመን በላይ ሊመረጥ አይችልም ። ይህ የጊዜ ገደብ በህገመንግስቱም ተደንግጎ ይቀመጣል ። መሪው የራሱን የስልጣን ዘመን ለማራዘም ይህን የህገመንግስት አንቀጽ በህዝብ ወይም በፓርላማ እንዳያስቀይር የሚከለክል የህግ አንቀጽ ይኖራል ።

5-7. ሁሉም በህግ አስፈጻሚዉ አካል ስር የሚዋቀሩ የስቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ከፖለቲካ ወገንተኝነ ነጻ ሁነው ይቋቋማሉ ። ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው በህግ ይደነገጋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

## 6. የፌደራል ወሰን አከላለል

6-1. የፌደራሉ ወሰን አከላለል ባህልን ፤ ልምድን ፤ ምጣኔ ሀብትን ፤ ታሪክንና መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ መስፈርትን ያማከለ ይሆናል ።

6-2. የሀገሪቱ የስራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል ። ሀገሪቱ እንደአስፈላጊነቱ በህዝብ ድምጽ ውሳኔ ሁለተኛ የስራ ቋንቋ ሊኖራት ይችላል ።

6-3. የፌደራል መንግስትና የክፍለሀገር አስተዳደሮች በህገመንግስቱ የተወሰነ የስልጣን ገደብ ይኖራቸዋል ። አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ በህግ ይደነገጋል ። የሃገሪቱ ህገመንግስት የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው ።ማንኛውም አዋጅና የአስቸኳይ ጊዜ መመሪያ ከዚህ ህገመንግስት አንቀጾች ጋር በማይቃረን መልኩ ይደነገጋል ። እነዚህን አንቀጾች የሚጻረር ሆኖ ሲገኝ ግን ተፈጻሚነት አየኖረውም ።

## 7. ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል ነው ። የሁሉም ዜጋ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት በህግ የተጠበቀ ይሆናል ። ሁሉም ዜጋ የማህበራዊ ደህንነቱና የስራ ዋስትናው በህግ የተረጋገጠ ነው ።

## 8. የብሄረሰቦች እኩልነት

**8-1. ብሄረሰቦች የራሳቸዉ ቋንቋ ፤ ባህል ፤ ሀይማኖት ፤ ወግና ታሪክ ተጠብቆላቸዉ** በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አንድነት በጋራ አብረው ይኖራሉ ፡፡

8-2. ማንኛውም በዘርና በሀይማኖት የተደራጀ ድርጅት ሀገር ለመምራት በፖለቲካ ውድድር ውስጥ እንዳይሳተፍ በህገመንግስቱ እንዲደነገግ ይደረጋል ።

## 9. የጾታ እኩልነት

9-1. ለዘመናት የኖረው ሴቶችን ዝቅ አድርጎ የመመልከት ኋላ ቀር ባህል ስር ነቀል የአመለካከት ለውጥ ያገኝ ዘንድ በትምህርት ቤቶች ፤ በእምነት ቤቶች ፤ በመገናኛ ብዙሀን ፤ በአርቲስቶችና በታዋቂ ግለሰቦች ከፍተኛ ትምህርትና ቅስቀሳ እንዲሰጥ አስፈላጊው ሁሉ ጥረትና ርብርብ ይደረጋል ። በመሆኑም ፓርቲያችን በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ የባህሪ ለውጥ እንዲደረግ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል ፡፡

9-2. ሴቶች በቅድመ ወሊድና ከወሊድ በኋላ ተገቢውን እንክብካቤና እረፍት ከክፍያ ጋራ እንዲያገኙ ይደረጋል ።

9-3. በሀገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት በጾታ ላይ የተመሰረተ የክፍያ ልዩነት እንዳይደረግ በህግ ይከለከላል ።

## *10. የሀይማኖት ነጻነትና እኩልነት*

መንግስት በሀይማኖት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንዳይገባ በህግ ይደነገጋል ። ሁሉም ሃይማኖቶች በእኩልነት ላይ የተመሰረተ በመከባበር መንፈስ አብረው እንዲኖሩ ጥረት ይደረጋል ። ሁሉም ሀይማኖቶች በነጻነት የአምልኮ ስራቸውን እንዲያካሄዱ ይሆናል ።

## 11. መገናኛ ብዙሀን

በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የጋዜጣ የሬዲዮ የቴሌቪዥንና የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያወች ያለምንም ተጽእኖ በነጻ ይደራጃሉ ይሰራሉ ። መንግስት ለሁሉም የመገናኛ ብዙሀን

ዜና የማስተላለፍ ግዴታ ይኖረዋል ። የግል ሚዲያወች እንዲቋቋሙ ይፈቀዳል ። አስፈላጊውን የህግ ጥበቃና ዋስትናም ይሰጣቸዋል።

## 12. የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ

12-1. ገበያ መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንከተላለን ። ሆኖም መንግስት መሰረታዊ በሆኑ የአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ ህዝቡ እንደየ አቅሙና ችሎታው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በከፊል ወይም በሙሉ ተሳታፊ ይሆናል ።

12-2. የሀገሪቱ የግል ባለ ሀብቶች ያላቸውን መዋእለ ንዋይ በስራ ላይ እንዲያውሉ በሁሉም ዘርፍ ቅድሚያ ያገኛሉ ።

12-3. የዉጭ ባለሀብቶች የሀገሪቱ ባለሀብቶች በማይሸፍኗቸው የኤኮኖሚ ዘርፎች መዋእለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ይበረታታሉ ። ለንብረታቸውም ህጋዊ ዋስትና ይሰጣቸዋል ።

## 13. የመሬት ፖሊሲ

13-1. ዜጎች የእኔ የሚሉት የእራሳቸዉ መሬት ሊኖራቸው ይገባል ። ይህን መሬት የመሸጥ የመለወጥና በወለድ አገድ የማስያዝ ወይም የማከራየት ሙሉ መብት ይኖራቸዋል ።

13.2 ለዘመናት ከሞፈር ቀንበር ያልተላቀቀውን የአስተራረስ ዘዴ በጥናት ላይ የተመሰረተ እንዱስትሪውን ሊያሳድግና ሊያጎለብት በሚችል መልኩ ወደ ዘመናዊነት እርሻ ይቀየራል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

## 14. ንግድና እንዱስትሪ

14-1. በአፍሪካም ሆነ በአለም ነጻ ንግድ ስምምነት መሰረት የህዝባችንና የሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስጥብቅ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አዲስ የንግድ ልውውጥ ስምምነት እንዲፈረም ይደረጋል ።

14-2. ከላይ በተራ ቁጥር 13-2. እንደተጠቀሰው ግብርናውን የሚያግዝ ነገር ግን በጥቃቅንና ዘመናዊ መንገድ የሚደራጅና በነጻ ገበያ መርህ የሚመራ ዘመናዊ የእንዱስትሪ ፖሊሲ እንከተላለን ።

14-3. የሀገሪቱ ብሄራዊ ባንክ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ሂሳብ አያያዝ ፣ ወለድ አሰባሰብና በቂ ተጠባባቂ ንብረት እንዲኖረው ይደረጋል ። እንዲሁም በርካታ ተጨማሪ ንግድ ባንኮች እንዲከፈቱና በመላው ሀገሪቱ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል ። የግል ባንኮችም እንዲቋቋሙ ተገቢው የማበረታቻ እርምጃ ይወሰዳል ።

## 15. የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት ፖሊሲ

በሀገሪቱ ከርሰ ምድር ውስጥና ውጭ ያሉ መአድን ፣ ደን ፣ የዱር አራዊት ፣ ውሀና ነዳጅ በመንግስት ቁጥጥር ስር ይሆናሉ ። መንግስት እነዚህን የተፈጥሮ ሀብቶች አቅም ከአላቸው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር አብሮ በጋራ ያለማል ።

## 16. የትምህርት ፖሊሲ

ሁሉም የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች በመንግስት ትምህርት ቤቶች በነጻ ይሰጣሉ ። የዩኒቨርሲቲ ትምህርት እንደየ ተማሪው አቅም እየተገመገመ በክፍያ፣ በድጎማና በነጻ እንዲሰጥ ይደረጋል ። ከዚህ በተጓዳኝ መንግስት የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማትን ያቋቁማል ።

## 17. የጤና ፖሊሲ

እርጉዝ ሴቶች ፣ ህጻናት ፣ እናቶች ፣ አሮጊቶችና አዛውንቶች በመንግስት ሆስፒታሎች በነጻ እንዲታከሙ ይደረጋል ። ከእነዚህ ውስጥ በቂ ገቢ ያላቸውና አቅማቸው

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

የሚፈቅደው እየተመረጡ በግል የጤና መድህን እንዲገቡ ይሆናል ። በሀገሪቱ ውስጥ የጤና መድህን እንዲስፋፉ ተገቢው ማበረታቻና እገዛ ይሰጣል ።

## 18. ባህል ባህላዊ እሴቶችና ቅርሶች

ባህልና ኪነጥበብ የማንነት መገለጫ እሴቶቻችን ስለሆኑ መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት ይንከባከባቸዋል ።

## 19. እስፖርት

ጤናማና ምርታማ ህብረተሰብ እንዲኖር እስፖርት የዘርፉ ምሰሶና ማገር ነው፡፡ ስለሆነም ጠንካራና በራስ የመተማመን ብቃት ያለው ትውልድ ለማፍራት መንግስት አንድ ጠንካራ የስፖርት ኮሚሽን ያቋቁማል ።

## 20. የውጭ ፖሊሲ

የአገራችን ጥቅምና ደህንነት የሚያስጠብቅ ሆኖ በገለልተኛ መርህ በመከባበርና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የውጭ ፖሊሲ እንከተላለን ። ሁሉንም አለም አቀፍ ውሎችና የሰብአዊ መብት ድንጋጌወች እንቀበላለን እናከብራለን ።

## 21. የመከላከያ ፖሊሲ

የሀገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት የፖለቲካ ወገንተኝነት የማይከተል ተጠሪነቱ ለሀገሪቱ ህገመንግስት ብቻ የሆነ ጠንካራና ዳር ድንበር አስከባሪ ሰራዊት ይሆናል ።

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

## 22. ፖሊስ

የሀገሪቱን ህገመንግስት የሚያከብርና የሚያስከብር ዜጎቿን ያለአግባብ የማያስርና የማያንገላታ የሀገር ውስጥ ሰላምና ጸጥታ አስከባሪ የፖሊስ ሰራዊት ይኖራል ።

## 23. ደህንነት

የሀገሪቱን ብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም ከውጭ ሀይላት ጉዳት የሚከላከልና የሚጠብቅ ሀገር አቀፍ የደህንነት መዋቅር ይኖራል ። ይህ ተቋም ማናቸውንም አይነት በሀገር ህልውና ላይ የሚቃጡ ሀገር በቀል ጥቃቶች ጭምር ይከላከላል ያከሽፋል ።

## 24. ማጠቃለያ

ኢሕብፓ በፕሮግራሙ ላይ ለሰፈሩት ራእዩና አላማወቹ መሳካት ያላሰለሰ ትግል ያደርጋል ። ይህውም በአላማ ከሚመሳሰሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ፤ ከሲቪክ ማህበራት ፤ ከሀገር ወዳዶችና ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ተሰልፎ አስፈላጊውን ሁሉ መስዋእትነት እየከፈለ ትግሉን ከግብ ለማድረስ በሀገሪቷና በህዝቡ ስም ቃል ይገባል ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ**

**nile@epnp.info**